*ቀስተደመና ሬድዮ*

*ትችት*

*(ከመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ የስነጽሁፍ ዝግጅት ክፍል የቀረበ)*

*(15.03.02)*

# *የአማራጭ ያለህ!*

በወያኔዎች ያንጃዎች ትርምስና በወጣቱ እንቅስቃሴ ሳቢያ ተሟሙቆ የነበረው የፖ
ለቲካ ሁኔታ ዛሬ ደብዛው እየጠፋ በአንድ በኩል መለስ ዜናዊ ስልጣንን ለጊዜውም ቢሆን
ጠቅልሎ የሚቆጣጠርበትና በሌላ በኩል ደግሞ የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ ቀዝቀዝዞና ግራ
የተጋባ መስሎ የሚታይበት ሁኔታ ውስጥ ገብተን ነበር። አሁን ደግሞ በባህር በራችን ጉዳ
ይ በሰፊ ህዝባዊ ደረጃም ባይሆን እንኳን በያንስ በፖለቲካ ሃይሎችና በሲቪክ ስብስቦች አ
ካባቢ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተከሰተ እናያለን።

የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ እነመለስና ኢሳያስ አፈወርቂ ከወዲሁ ያውቁታል። ችግራ
ቸው ሌላ ምንም ሳይሆን ከባድመ፣ ጾሮራና ዛልአንበሳ አልፎ የኢትዮጵያን ህጋዊና ታሪካዊ
መብት አስከብሬ የባህር በሩዋን አስመልሳለሁ እያለ ለሚታገለው ሃይል አነሰ ሲሉት ተቀ
ነሰ እንዲሉ አልፎ ተርፎ ከኢትዮጵያ ግዛቶች ተቆርሰው ለኤርትራ ተሰጥተዋል፣ የተወሰኑ
ኢትዮጵያውያን ደግሞ ዜግነታቸው ተሰርዞ ኤርትራዊ እንዲሆኑ «ተፈርዷል» የሚለውን
ውሳኔ እንዴት አርገው እንደሚያቀርቡት ብቻ ነው።

በዚህ በሚቀሰቀሰው ህዝባዊ ቁጣ ሳቢያ ወያኔዎች ከፍተኛ የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ
ሊገቡ ይችላሉ። ነገር ግን ዛሬ ተቃዋሚዎች በአሉበት ሁኔታ ይህ ተገቢ የህዝብ ቁጣ እን
ደአምናው ከፍተኛ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ቢወልድም እንኳ ድርጅታዊ አቅሙም፣ አማራጭ
መፍትሄውም ኖሮት ለዚህ ንቅናቄ አመራር ሊሰጥ የሚችል ሃይል ከሌለ ልክ እንዳምናው
የህዝቡ ንቅናቄ አቅጣጫና አመራር አጥቶ በወያኔዎች ተንኮል ከቁጥጥር ውጭ የሚሆንበ
ትና እንደገና ለመመታት የሚመችበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። በባህር በራችን ጉዳይ እ
የተነሳሳ ያለውም እንቅስቃሴ እንደሌሎቹ የቀደሙት እንቅስቃሴዎች ቀስ በቀስ አሁን ያለ
ውን ስፋትና ጥልቀት ሊያጣ ይችላል። ይህ እንዳይሆን ከተፈለገ ለትግሉ መስፋትና ቀጣይ
ነት ሲሉ ዛሬ በመንቀሳቀስ ላይ ያሉት ምሁራን፣ ዴሞክራቶች፣አገር ወዳዶች፣ የፖለቲካና
የሲቪክ ድርጅቶች አሁን በሚያሳዩት የትግል ወኔ ከዚህ ትግልህ ዝባችንን አደባልቀው ለ
መቀጠል የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚና ማህበራዊ አማራጮች አቅርበው የህዝቡን ት
ግል አቅጣጫ ማስያዝ አንገብጋቢ ጥያቄ ይመስለናል።

በአለፈው መስከረም ወር የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) ባወጣው
አንድ ሰፊ ጽሁፍ ላይ ተቃዋሚ ሃይሎች አንድ የጋራ በሆነ ሰነድ ዙሪያ አንድ የሽግግር
አማራጭ ማቅረባቸው ምን ያህል የሞት ሽረት ጥያቄ እንደሆነ ለመጠቆም ተሞክሯል። በ
ቅርቡ ደግሞ ኢህአፓ ተቀዋሚዎች ተሰባስበው አንድ የሽግግር መንግስት እንዲመሰረት እ
ንዲታገሉ ጥሪ አድረጉዋል። ተቃዋሚ ሃይሎች ምንም ይሁን ምንም መክረውና ዘክረው አ
ንድ የጋራ ሰነድና አቅጣጫ መያዛቸው፣ ይህንን ሰነድ በተግባር ለመተርጎም አንድ የጋራ
አካል መመስረታቸው ጠቃሚም አስፈላጊም አንገብጋቢም ነው። ግን በሌሎች በሌሎች ህ
ዝባዊ ጥያቄዎችና ዴሞክራሲያዊ አማራጮች ዙሪያ የህዝባችን ትግል አይሎ ወያኔዎችንና
ስርአታቸውን አስጨንቆ የሚይዝበት ደረጃ ካልተደረሰ በስተቀር በጋራ ሰነድና በጋራ አካ
ል ዙሪያ ብቻ ታግሎ ወደፊት ብዙ መግፋት ይቻላል ማለት ትልቅ ኢሉዥን ነው። ለዚ
ህም ሁለት የተያያዙ ምክንያቶች አሉት።

አንደኛው ምክንያት ይህ በህብረት የሚደረገው ትግል ዴሞክራሲ፣ የህግ የበላይነት ፣ ነጻ ምርጫ፣ ብሄራዊ ውይይት፣ ሁሉን አቀፍ አገራዊ ጉባኤ፣ የዴሞክራታይዜሽን ካውን ስል ወዘተ ወያኔ በህዝብ ትግል ተገድዶ የሚቀበላቸው ወይም ደግሞ በዚሁ በአየለ የህዝብ ተጋድሎ ማእበል ታልፎ ሲሄድ በዚህ አጥፊ ሃይል መቃብር ላይ እውን የሚሆኑ ስትራቴ ጅያዊ አላማዎች ናቸው። ህዝባችን በእለት ተእለት ችግሮቹ ተወጥሮ እለት ከእለት ከሚ ያቀርባቸው ተጨባጭ ጥያቄዎችና እለት ተእለት ከሚያካሂዳቸው ግብታዊ ትንንቆች ጋር እምብዛም ግንኙነት የላቸውም።

ሁለተኛ የሩቅ ጊዜና የትግላችን መዳረሻ ላይ የሚገኙ ስትራቴጂያዊ ድሎች ናቸው ካልን እዚህ የድል ደረጃ የምንደርሰው እንዴት ነው ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል ። ለዚህም መልሱ ግልጽ ነው። እነዚህ ክቡር አላማዎች ለወያኔ እንደማመልከቻ አይቀር ቡም። የባእዳን ሃያላንም ምልጃ አያራምዳቸውም። አንዱና ብቸኛው መፍትሄ የህዝቡ ት ግል አይሎ አንድ የሆነ ደረጃ መድረሱ ነው። የህዝባችን ትግል እዚህ ደረጃ ሲደርስ፣ ወ ያኔ በህዝቡ ትግል ተወጥሮ ሲያዝ፣ በሃገር ደረጃ ቀውስ ሲፈጠር ያኔ እነዚህ ከአሁኑ በግ ልጽ የተቀመጡ የጋራ ሰነዶቻችን ለኢትዮጵያም ህዝብ፣ ለአለም አቀፉም ኮሙኒቲ፣ ግራ ለሚጋባው የኢህአዴግ አባልና ምናልባትም በቀውሱ ሳቢያ ለሚከፋፈለው የኢህአዴግ አመ ራር፣ ለሰራዊቱ፣ ለፖሊሱ ወዘተ እንደተጨባጭ «የቀውስ መውጫ» መፍትሄዎች ሊቀር ቡ ይችላሉ። ይህ ሲሆን ደግሞ በትግል ላይ ላለው ህዝብም ሆነ ሌላ ገና ትግሉን ላልተደ ባለቀው ክፍል የጋራ መፈክር ሆነው ቀርበው የማይበገሩ የትግል መሳሪያ ሊሆኑ ይችላሉ።

ይህ ስለተባለ ግን ተቃዋሚ ሃይሎች በጣም በአስቸኳይ በአንድ የጋራ ሰነድ ዙሪያ አንድ የጋራ አማራጭ ይዘው መንቀሳቀስ የለባቸውም ማለት አይደለም። መጀመሪያ ሌላው ቢቀር ካሁኑ በእዚህ አማራጭ ዙሪያ ተደራጅቶ በህብረት ቅስቀሳ ማድረግ ለትግሉ አንድ አቅጣጫ ከመስጠቱ በላይ የህዝቡንም የትግል ሞራል ሊያነሳሳ ይችላል። ሁለተኛ አምና በአንጃዎቹ ትርምስም ሆነ በወጣቱ ንቅናቄ ሳቢያ እንደታየው አሁን ደግሞ በድንበር ኮሚ ሽኑ ኢፍትሃዊ ውሳኔ ሳቢያ ልንጠብቅ እንደምንችለው አንድ ቀውስ ቢከሰት ቀደም ሲል የቀረበ፣ ህዝቡ የሚያውቀው፣ ተቃዋሚ ሃይሎች ሁሉ በጋራ የተሰለፉበት አንድ «ከቀውስ የመውጫ» አማራጭ ከአለና ሁሉም በጋራ ይህንን አማራጭ በእንቅስቃሴ ላይ ለሚገኘው ሃይል ማስጨበጥ ከተቻለ ትግሉ ከመክሰም ይልቅ የሚፋፋምበትን ሁኔታ አመቻቸን ማለት ነው። ሶስተኛ የእንደዚህ አይነቱ የጋራ አማራጭ ከዛሬው መቅረብ ከዚህ ቀውስ ወያኔ እን ደገና በአሸናፊነት እንዳይወጣ ወይም ደግሞ እንደለንደኑ ጉባኤ ጊዜ አንድ በባእዳን ድጋፍ ና አስተባባሪነትም ሆነ በሌላ ታሪካዊ አጋጣሚ ጊዜያዊ የበላይነትን የያዘ ሃይል ወይም ቅን ጅት ስልጣን እጠቀልላለሁ ብሎ የሃገራችን ነገር «ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ» እንደተባለው እ ንዳይሆን ስለሚረዳ ይህ የጋራ ሰነድና ይህ የጋራ አማራጭ እጅግ አስፈላጊ ነው።

ችግሩ እዚህ ላይ ሳይሆን ይህንን የጋራ ስትራቴጂያዊ አላማ በተግባር ለመተርጎም የሚያስፈልገውን የሃይል ሚዛንና የፖለቲካ ቀውስ እንዴት አድርገን እንፍጠረው ለሚለው መሰረታዊ ጥያቄ አጥጋቢ መልስ አለማግኘታችን ነው። በኛ ግምት ይህንን የሃይል ሚዛን መፍጠር የምንችለው በሁለት ተዛማጅ በሆኑ ሂደቶች ነው። መጀመሪያ በያለበት በተለያዩ ጥያቄዎች ዙሪያ በተለያዩ ግዜያቶች ከሞላ ጎደል በግብታዊነት እየተካሄዱ ላሉት የህዝባ ችን ትግሎች ግልጽ የሆኑ አማራጮች አቅርቦ ቀጣይነታቸውንና ቅንብራቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ሁለተኛ በዚህ መልክ ሰራተኛው፣ ነጋዴው፤ ገበሬው፣ የሃገራችን ኢንቫስተር ፣ አሰሪው፣ አምራቹ፣ ተማሪውና ሌላው የህብረተሰብ ክፍል የሚጨነቅበትን ጥያቄ አንስ ቶ ሲታገል ሁሉም ለሃገሪቱ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ያመጣሉ የምንላቸውን የጋራ መፈክሮ ቻችንን ከትግል አላማው ውስጥ እንዲያካትት ማድረግ ያስፈልጋል። ይህንን ካደረግን ከነ ዚህ የተሰበጣጠሩ ትግሎች ወያኔ በምንም ሊበግረው የማይችል ዴሞክራሲያዊ የትግል ማ እበል እንፈጥራለን ማለት ነው።

ሁለቱን ትግሎች በዚህ መልክ ለማዋሃድና ለማቀናጀት ዛሬ ዋና አንገብጋቢ ተግባራ ችን ሃገራችንንና ህዝባችንን ከእለት እለት እያፈራረሱና እያደቀቁ በመሄድ ካሉት መሰረታ

ዊ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ስርአት ጥያቄዎች አንጻር አማራጭ አቅርቦ የህዝባችንን ትግል ጥራትና አቅጣጫ የመስጠቱ ተግባር ይመስለናል። እዚህ ላይ ብዙ ሰው «ተቃዋሚዎች ግልጽ አማራጭ ይዘው ወያኔን ሲታገሉ አመታት አለፋዋቸው አይደለም ወይ?» ብሎ ሊጠይቅ ይችላል። በኛ በኩል ግን መልሱ አጭር ነው። የአማራጭ ችግር አለ።

1ኛ. በአንድ በኩል ሲታዩ የሚቀርቡት «አማራጮች» ወይ የተድበሰበሱ፤ ድፍንና ስትራቴጂያዊ ሆነው በኛና በወያኔዎች መሃከል ያለውን ትግል ያልለየለት «የአህያ ውድቂያ» አይነት አሸናፊና ተሸናፊ በግልጽ የማይለዩበት ትግል የሚያስመስሉ አማራጮች ናቸው። ነጻ ምርጫ፣ የህግ የበላይነት፤ ዴሞክራሲ፣ ሌላው ቀርቶ የሃገር አንድነት እንደአማራጭ ሲቀርቡ ወያኔዎች በነዚህ አማራጮች አናምንም አይሉም። እንዲያውም ከተቃዋሚዎች ይልቅ እኛ በተግባር እየተረጎምናቸው ነው ይላሉ። በዚህ መልክ ተቃዋሚዎች አቀረብን የሚሉት «አማራጭ» በጣም አሻሚ ስለሚሆን ለምሁሩና ለነቃው ክፍል እንጂ በሚልዮን በሚቆጠረው ህዝብ ፊት የማያወላዳ የፖለቲካ የበላይነት ስለማይሰጠን የትግል መሳሪያነቱ ጉዳይ እጅግ አጠራጣሪ ነው።

2ኛ. ብዙ ተቃዋሚዎች በርእዮተአለም ምርጫም ሆነ ነጻ ምርጫን፣ ዴሞክራሲን፣ ብሄራዊ ውይይትን ወዘተ ተግባራዊ ለማድረግ በባእዳን ሃያላን ላይ በጣሉት «ተስፋ» የተነሳ ዛሬ ገበሬው፣ ሰራተኛው፤ ነጋዴው፤ ተማሪው፤ ለሚያነሳው ጥያቄ መልስ እንዳይሰጡ የፍጥኝ የታሰሩበት ሁኔታ ውስጥ ያሉ ይመስላል። ፕራይቬታይዜሽንና ስትረክቸራል አጀስትሜንት በደርዘን ሽ የሚቆጠሩ ወዛደሮችን ለጅብ ሲዳርጉ፣ በነአይኤም ኤፍ ግፊት በመጠንኛ ዋጋ ድሃው በልቶ እንዲያድር ደርግ ያካሄደው የነበረው የዋጋ ድጎማ ፖሊሲ ሲፈርስ፣ የህክምናና የትምህርት አገልግሎቶች ሲቀነሱ፣ ገበሬው በማዳበሪያና በመድሃኒት ስም በምእራቡ አለም የተከለከሉ ኬሚካልስ እየገዛ መሬቱን እንዲበክል እሱም አዳ ውስጥ እንዲዘፈቅ ሲደረግና በቅርቡ አንድ ካናዳዊ ምሁር እንዳጋለጡት በነጻ ገበያ ስም «በኢትዮጵያ የርሃብ ዘር ሲዘራ» በአዲሱ የግሎባላይዜሽን ፈሊጥ ሃገራችን ታዳጊ ኢንዱስትሪዎቿን እንዳትንከባከብ ተደርጋ ከቻይና የሚመጡ ጫማዎች ገበያ እየፈሰሱ በሃአገሪቱ ካሉት የጫማና የቆዳ ውጤት አምራች ድርጅቶች ግማሾቹ እንዲዘጉ ሲደረግና አስራ አምስት ሽህ ወዝአደሮች ለርሃብ ሲዳረጉ በዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ የንግድ ምክር ቤት «መንግስት ለሃገሪቱ አምራቾች ጥበቃ ማድረግ አለበት» ብሎ አቤት ለማለት ሲገደድ፣ ሀገሪቱን እንረዳለን ብለው የገቡ «ግብረ ሰናይ» ድርጅቶች «አይል ሞንተራይዜሽን» በሚል ፈሊጥ ርካሽ ዘይት እያስገቡ ገበያ ላይ በማፍሰስ የሃገሪቱን ዘይት አምራቾች ለኪሳራ ሲዳርጉ .... ባጭሩ ገበሬው፣ ሰራተኛው፣ ነጋዴው የሚያቀርባቸውንና ዞሮ ዞሮ በመተከል ላይ ያለውን «የነጻ ገበያ» ተብየ ኢኮኖሚና አለም አቀፉን ስርአት የሚጻረሩ ጥያቄዎችን የሚያስተናግድና ሌላ አማራጭ ፖሊሲ ይኸውልህ የሚል ተቃዋሚ ሃይል አይታይም።

ይህ እስከሌለና ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች «በእናንተ ጉዳይ የወያኔዎች ፖሊሲ ይኸ ነው። እኛ ደግሞ ከነዚህ ተጨባጭ ጥያቄዎቻችሁ አንጻር ከወያኔዎች ፖሊሲ የተለየ ይኸ አቋም አለን» የሚል የፖለቲካ ሃይል እስከሌለ ድረስ ወያኔዎች ከፖለቲካው አንጻር ድል ተመቱ ማለት ራስን ማታለል ነው። ግልጽ የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚና የማህበራዊ አማራጭ ጠፍቶ ተቃዋሚ ሃይሎች የበላይነትን ባልተጎናጸፉበት ሁኔታ ደግሞ ነጻ ምርጭ፣ የህግ የበላይነት፣ ዴሞክራታይዜሽን እያልን የምናካሂደው ትግል ላለፉት አስር አመታት እንዳልሰራ ሁሉ በመጭዎቹም አመታት ሃገራችንን ከጥፋትና ከውድመት አትርፎ የሰላም፣ የብልጽግናና የፍትህ ምድር ያደርጋታል ማለት እጅግ አደገኛ ህልም ይመስለናል።

መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ
የጽንጽሁፍ ዝግጅት ክፍል
መጋቢት 6 ቀን 1994 ዓ.ም
(15.03.02)